የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፴፰
አዲስ አበባ- ሰኔ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No. 38
ADDIS ABABA- 24th June. 2005


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፬፻፶/፲፱፻፺፯ ዓ.ም

የፌዴራል የከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅ ...ገጽ ፫ሺ፩፻፱


## አዋጅ ቁጥር ፬፻፶/፲፱፻፺፯

## የፌዴራል የከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በሀገሪቱ ውስጥ በዕቅድ ላይ የተመሰረተ የከተሞች ልማት እንዲኖር የከተማ ፕላን አገልግሎት እንዲስፋፋ ማድረግ በአጠቃላይ ብሔራዊ የልማት ጥረት ውስጥ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ቁልፍ ተግባር ሆኖ በመገኘቱ፣

አዳጊ ከተሞች ወቅታዊ የሆኑ የፕላን መርሆዎችን በመከተል ጤናማና ዘላቂ የከተማ ልማት እንዲኖራቸው ለማድረግ በከተማ ፕላን የሚመሩበትን ሥርዓት መደንገግና የአቅም ግንባታ ድጋፍ የሚሰጥበትን ሁኔታ ማመቻቸት ጠቃሚ ሆኖ በመገኘቱ፣

በሀገሪቱ ውስጥ ካለው ያልተማከለ አሠራር ጋር በሚጣጣም መልኩ የከተማ ፕላንን በሚመለከት የፌዴራል መንግሥቱን አካል እንደገና ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የፌዴራል የከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፶/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

CONTENTS


Proclamation No. 450 /2005

Federal Urban Planning Institute Establishment Proclamation ........ Page 3109


## PROCLAMATION NO. 450 /2005.

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE FEDERAL URBAN PLANNING INSTITUTE

**WHEREAS,** it is found prudent to promote the provision of urban planning services in the Country since the planned development of the Country's urban centers has more than ever become a key task in the overall national development efforts;

**WHEREAS,** it is found important to define, ir accordance with the state-of-the art urban planning principles, a system that would ensure a healthy and sustainable development of growing urban centers as well as to facilitate the provision of capacity building supports;

**WHEREAS,** it is found necessary to re-establish the organ of the Federal Government that is entrusted with urban planning mandates consistent with the decentralized systems put in place in the Country;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution, of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows;

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Federa: Urban Planning Institute Establishment Proclamation No. 450/2005."


ያንዱ ዋጋ 2·80
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩/ "ሚኒስትር" ወይም "ሚኒስቴር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ወይም ሚኒስቴር ነው፣

፪/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ አስተዳደሮችን ይጨምራል፣

፫/ "የከተማ ፕላን" ማለት አግባብ ባላቸው የከተማ ፕላን ሕጎች ውስጥ የተመለከቱትን የከተማ ፕላን ዓይነቶች የካትታል።

## ፫. መቋቋም

፩/ የፌዴራል የከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪/ የኢንስቲትዩቱ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

## ፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

## ፭. የኢንስቲትዩቱ ዓላማ

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፣

፩/ የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸምን በሚመለከት ለክልሎች፣ ለከተሞችና ለግሉ ዘርፍ የአቅም ግንባታ እገዛ የማድረግ፣

፪/ የከተማ ፕላንን በሚመለከት የምክር አገልግሎት የመስጠት፣

፫/ የከተማ ፕላንን እንዲሁም ሌሎች መሠረታዊ ከተማ ነክ መረጃዎችን በተመለከተ የመረጃ ማዕከል ሆኖ የማገልገል፣ እና

፬/ ከተሞች በፕላን የሚመሩ፣ ከአካባቢያቸው ገጠር ጋር ጠንካራ ቁርኝት ያላቸውና የፈጣን ልማት ማዕከላት እንዲሆኑና የተመጣጠነ የአከታተም ሥርዓት ለማምጣት የሚያስችል ከተማ ፕላን የማዘጋጀት፣

## 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "Minister" or " Ministry" means the Minister or Ministry of Federal Affairs, respectively;

2/ "region" means any region referred to in Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the administrations of Addis Ababa and Dire Dawa;

3/ "urban plan" means the different urban plan typologies prescribed in the relevant urban planning laws.

## 3. Establishment

1/ The Federal Urban Planning Institute (hereinafter "the Institute") is hereby established as an autonomous public organ having its own legal personality.

2/ The Institute shall be accountable to the Ministry.

## 4. Head Office

The Institute shall have its head office in Addis Ababa and may establish branch offices elsewhere as may be necessary.

## 5. Objectives

The Institute shall have the following objectives:

1/ to provide capacity building support to regions, urban centers and the private sector on matters pertaining to urban plan preparation and implementation;

2/ to provide urban related consultancy services;

3/ to serve as an information hub on urban planning and other basic urban related information; and ;

4/ to achieve a balanced urban system by way of preparing integrated urban plans that encompass socio-economic and land-use dimensions and that ensure plan-led development of urban centers that have strong linkages with their rural hinterlands and serve as centers of rapid development.

## ፮. ሥልጣንና ተግባር

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩/ የአቅም ግንባታ አገልግሎትን በሚመለከት፣

ሀ/ ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የከተማ ፕላን የማዘጋጀትና የማስፈፀም አቅማቸው እንዲጐለብት የአደረጃጀትና የአሰራር ማሻሻያ ምክር ይሰጣል፣

ለ/ የከተማ ፕላን በማዘጋጀትና በማስፈጸም ሥራ ላይ ለተሰማሩ የክልልና የከተማ አስተዳደር ባለሙያዎችና ለግሉ ዘርፍ አጫጭር ሥልጠናዎችና የሥራ ላይ ሥልጠናዎች ይሰጣል፣

ሐ/ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የከተማ ፕላን ሥራ መልካም ልምዶችን ቀምሮ ያሠራጫል፣

፪/ የምርምርና የምክር አገልግሎትን በሚመለከት፣

ሀ/ ከክልሎችና ከከተማ አስተዳደሮች ጋር በመተባበር የፕላን አዘገጃጀት ሥርዓቱን ለማሻሻል በፀደቁ የከተማ ፕላኖች አፈጻጸም ላይ የክትትልና ግምገማ ሥራዎችን ያከናውናል፣ መልካም ልምዶችን ይቀምራል፣

ለ/ የከተማ ፕላኖችን ለማዘጋጀት የሚረዱ ሁለገብ ጥናትና ምርምሮች ያካሂዳል፣

ሐ/ የከተማ ፕላንን በሚመለከት የፌዴራል መንግሥቱን ያማክራል፣

መ/ የከተማ ፕላንን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ለተለያዩ ተጠቃሚዎች የምክር አገልግሎት ይሰጣል

፫/ የከተማ ነክ መረጃ አገልግሎትን በሚመለከት፣

ሀ/ የከተማ ፕላን መረጃ እንዲሁም የከተማ ነክ መሠረታዊ መረጃዎች ማዕከል በመሆን ያገለግላል፣

ለ/ ከተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት መሠረታዊ ከተማ ነክ መረጃዎች ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ያሠራጫል፣

፬/ የከተማ ፕላን ዝግጅትን በሚመለከት፣

## 6. Powers and Duties

The Institute shall have the following powers and duties:

1/ in the area of capacity building:

a/ to provide advise to regions and urban administrations on changes to be introduced in terms of organizational structures and working systems and procedures with a view to enhancing their urban plan preparation and implementation capacity;

b/ to provide short and on-the –job training to staff working in region government and urban;

c/ to formulate best practices by reviewing local and international experience in urban planning and disseminate same.

2/ in the area of research and consultancy:

a/ to undertake follow-up and evaluation studies, in collaboration with regions and urban administrations, on the implementation of approved urban plans with a view to improving urban planning methods and working procedures and to formulate best practices in urban planning;

b/ to conduct multi-disciplinary studies and researches that serve as basis for the preparation of urban plans;

c/ to advise the Federal Government on matters that pertain to urban planning;

d/ to provide consultancy services on matters related to urban planning to persons seeking such services;

3/ in the area of information support services:

a/ to serve as information hub for urban planning as well as other basic urban related information;

b/ to collect, collate and disseminate basic urban related information from the concerned governmental and non-governmental institutions;

4/ in the area of urban plan preparation:

ሀ/ በክልሎችና ከተሞች ሲጠየቅ ራሱ ወይም እንዳስፈላጊነቱ ከግል ወይም ከመንግሥት ተቋማት ጋር በመቀናጀት ለከተሞች ፕላን ያዘጋጃል፣

ለ/ የመሬት ላይ ቅየሣ፣ የአየር ፎቶግራፍ እና ሌሎች ዘዴዎችን በመጠቀም ለከተማ ፕላን አገልግሎት የሚውሉ መሠረታዊ ካርታዎችን ያዘጋጃል::

ሐ እንስቲቱ ለክልሎችና ለከተማ አስተዳደሮች ለሚሰጠው አገለግሎት በሚኒስቴሩ የሚወሰን ሆኖ እስከ ግማሽ የአገልግሎት ዋጋ ክፍያ ድረስ ወጪ እንዲጋሩ ሊያደርግ ይችላል::

፯. <u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>

ኢንስቲትዩቱ፣

፩/ አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅና አንድ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ እና

፪/ አስፈላጊ ሠራተኞች፣
ይኖሩታል::

፰. <u>ስለ ዋናው ሥራ አስኪያጅና ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ</u>

የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ እና ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ በፌዴራል መንግሥት ይሾማሉ::

፱. <u>የዋናው ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩/ ዋና ሥራ አስኪያጁ ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ተግባራት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስኪያጁ፣

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ የተመለከተውን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፣

ለ/ በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች ሕጎችና በመንግሥት በሚወሰን የደመወዝ ስኬል መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

ሐ/ የከተማ ፕላንን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን እያዘጋጀ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣

a/ to prepare urban plans upon the request of regions and urban centers; and

b/ to prepare base maps to be used in the preparation of urban plans by employing ground survey, aerial photography and other appropriate techniques.

c/ concerning services the institute renders to regions and urban centers, regions and urban center in to a cost sharing arrangement to be determined by the ministers where by they covere up to half of the total cost of service provision.

**7. Organization of the Institute**

The Institute shall have:

1/ a General Manager and a Deputy General Manager; and

2/ the necessary staff.

**8. The General Manager and the Deputy General Manager**

The Federal Government shall appoint the General Manager and the Deputy General Manager of the Institute.

**9. Powers and Duties of the General Manager**

1/ The General Manager shall, subject to the general directives of the Ministry, direct and administer the activities of the Institute.

2/ Without limiting the generality of Sub-Article (1) of this Article, the General Manager shall:

a/ exercise the powers and duties of the Institute specified in Article 6 of this Proclamation;

b/ employ and administer personnel of the Institute in accordance with the federal civil service laws and the salary scale determined by the Government;

c/ draft and submit to the Ministry policies regarding urban planning and follow up the implementation of same upon approval;

መ/ የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም እና በጀት በማዘጋጀት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በሥራ ላይ ያውላል፣

ሠ/ ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

ረ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፣

ሰ/ የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊና ወቅታዊ የሥራ እንቅስቃሴና የሂሣብ ሪፖርቶች እያዘጋጀ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል::

፫/ ዋናው ሥራ አስኪያጅ ለኢንስቲትዩቱ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅና ለሌሎች ኃላፊዎች እንዲሁም ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል::

## ፲. የምክትል ዋና ሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር

የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩/ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፣

፪/ በኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

## ፲፩. በጀት

የኢንስቲትዩቱ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፣

ሀ/ በፌዴራል መንግሥት ከሚመደብ በጀት፣

ለ/ ኢንስቲትዩቱ ከሚያስከፍለው የአገልግሎት

ክፍያ፣ እና

ሐ/ ከማንኛውም ምንጭ የሚገኝ ዕርዳታና ስጦታ::

## ፲፪. ስለሂሣብ መዛግብት

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል::

፪/ የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ::

d/ prepare and submit to the Ministry the work program and budget of the Institute and implement same upon approval;

e/ effect expenditures in accordance with the approved budget and work program of the Institute;

f/ represent the Institute in all its dealings with third parties;

g/ prepare and submit to the Ministry the annual and periodic performance and financial reports of the Institute.

3/ The General Manager may, to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Institute, delegate part of his powers and duties to the deputy General Manager and other officials as well as the employees of the Institute.

## 10. Powers and Duties of the Deputy General Manager

The Deputy General Manager shall have the following powers and duties:

1/ to act on behalf of the General Manager during his absence;

2/ to perform other duties given to him by the General Manager.

## 11. Budget

The budget of the Institute shall be drawn from the following sources:

a/ budgetary allocation made by the Federal Government;

b/ service charges to be collected by the Institute; and

c/ assistance and grants to be obtained from any source.

## 12. Books of Accounts

1/ The Institute shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and other financial documents of the Institute shall be audited annually by the Auditor general or by auditors designated by him

## ፲፫. የተሻረ ሕግ

፩/ በብሔራዊ ከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፯/፲፱፻፹፯ በዚህ አዋጅ ተሽሯል::

፪ ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም::

## ፲፬. ደንብ ስለማውጣት

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለአዋጁ አፈጻጸም የሚረዱ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል::

## ፲፭. የመብትና ግዴታ መተላለፍ

በአዋጅ ቁጥር ፫፻፲፯/፲፱፻፹፯ ተቋቁሞ የነበረው የብሔራዊ ከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኢንስቲትዩቱ ተላልፈዋል::

## ፲፮. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

**አዲስ አበባ ሰኔ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፕሬዚዳንት**



## 13. Repeal

1/ The National Urban Planning Institute Establishment Proclamation No. 317/1987 is hereby repealed.

2/ No Proclamation, regulation, directive or practice, shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, have effect with respect to matters provided for in this Proclamation.

## 14. Power to Issue Regulations

The Council of ministers may issue Regulations for the Implementation of this Proclamation.

## 15. Transfer of Rights and obligations

The rights and obligations of the National urban Planning Institute established under Proclamation No. 317/1987 are hereby transferred to the Institute.

## 16. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the 24th day of June, 2005.

**Done at Addis Ababa, the 24th day of June,2005**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**